አላህ ወንጀሎችን የሚሰርዝበትን፣ ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር አልጠቁማችሁምን?

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አላህ ወንጀሎችን የሚሰርዝበትን፣ ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር አልጠቁማችሁምን?" ሶሐቦችም "እንዴታ የአላህ መልክተኛ" አሉ። እርሳቸውም "በአስቸጋሪ ወቅት ዉዱእን አዳርሶ ማድረግ፣ ወደ
መስጂድ እርምጃ ማብዛት፣ አንድ ሰላት ካለቀ በኋላ ሌላ ሶላት መጠበቅ፤ ይኸው ነው "ሪባጥ" (ዘብ መጠበቅ) ናቸው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለወንጀሎቻቸው መማር፣ ከጠባቂ መልአክት መዝገብ ወንጀላቸውን ለማሰረዝ፣ በጀነት ውስጥም ደረጃዎችን ከፍ ለማድረግ ምክንያት የሚሆኑ ስራዎችን እንዲጠቁሟቸው ይፈልጉ እንደሆነ ባልደረቦቻቸውን ጠየቋቸው። ሶሐቦችም: "አዎን እንፈልጋለን" አሉ። እሳቸውም እንዲህ አሉ: የመጀመሪያው: እንደ ቅዝቃዜ፣ የውሃ ማነስ፣ የሰውነት ህመምና አቃጣይ ውሃን የመሰሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ዉዱእን መሙላትና ማዳረስ ነው። ሁለተኛው: ከሩቅ አካባቢ በመነሳት ወደ መስጂድ እርምጃን ማብዛትና ደጋግሞ መመላለስ ነው። ሶስተኛ: የሶላትን ወቅት መጠበቅ፣ ልብን በሶላት ማንጠልጠል፣ ለሶላት መዘጋጀት፣ ጀመዓን ለመጠበቅ መስጂድ ውስጥ ለሶላት መቀመጥ፣ ከሰገደም በኋላ ለሌላ ሶላት መስገጃው ላይ ቁጭ ብሎ መጠበቅ ነው። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነዚህ ጉዳዮች ትክክለኛው ዘብ መጠበቅ እንደሆኑ ገለፁ። ምክንያቱም የሰይጣንን መንገዶች በነፍስ ላይ ስለምትዘጋ፣ ስሜትን ስለምታሸንፍ፣ ነፍስ ለወስዋስ ተገዥ እንዳትሆን ስለምትከለክል ነው። ነፍስን በማሸነፍ የአላህ ጭፍራ የሰይጣንን ሰራዊት ያሸንፉበታል። ትልቁ ጂሀድም ይህ ነው። ስለዚህ የዚህ ደረጃ ኬላ ላይ ጠላትን እንደመጠበቅ እንደሆነ አድርገው ገለፁት።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3574